**የአክሲዮን ማህበር ዓይነቶች፣ አደራጆች እና መስራቾች፡ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ባዘጋጀው ረቂቅ መመሪያ ላይ የቀረበ አስተያየት**

ሰርካለም እሸቴ[5297]

## 1. መግቢያ፡-

1. የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ***"የአክሲዮን ማህበራትን ክትትል፣ ድጋፍና ቁጥጥር ለመደንገግ የወጣ መመሪያ"*** (ከዚህ በኋላ "***ረቂቅ መመሪያ***" ተብሎ ይገለጻል) በሚል ረቂቅ መመሪያ አዘጋጅቶ ባለድርሻ አካላት አስተያየት እንዲሰጡበት ለህዝብ ግልጽ አድርጓል። ይህም በፌዴራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ድንጋጌዎች መሰረት የሚጠበቅ ነው። በረቂቅ መመሪያው መግቢያ ላይ እንደተመለከተው መመሪያው የአክሲዮን ማህበራትን የሚመለከቱ የአዲሱን ንግድ ሕግ ድንጋጌዎች በአግባቡ ለማስፈጸም ታስቦ የወጣ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መመሪያውን ያወጣው በንግድ ህጉ (አዋጅ ቁጥር 1243/2013) አንቀጽ 5 እና በአስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19 (4) መሰረት በተሰጠው መመሪያ የማውጣት ስልጣኑ ነው።

2. ረቂቅ መመሪያ በስምንት ክፍሎች የተዋቀረ ሲሆን በአጠቃላይ 47 አንቀጾችን የያዘ ነው። በዚህ አጭር ጽሑፍ ውስጥ ለመዳሰስ የተሞከረው ከአክሲዮን ማህበራት አመሰራረት ጋር በተያያዘ ስለአክሲዮን ማህበራት ዓይነቶች፣ ስለአደራጆችና መስራቾች የሚመለከቱትን የረቂቅ መመሪያውን ድንጋጌዎች ብቻ ይሆናል። በዋናነትም እነዚህ ድንጋጌዎች አግባብነት ካላቸው የአዲሱ ንግድ ህግ ድንጋጌዎች ጋር ምን ያክል የተጣጣሙ ናቸው የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ አስተያየት ለማቅረብ ተሞክሯል።

## 2. አስተያየት፡-

3. በአዲሱ የንግድ ህግ መሰረት አክሲዮን ማህበራት ከሚቋቋሙበት ሂደትና መስፈርቶች አኳያ አክሲዮኑ ለሕዝብ ክፍት የሆነ የአክሲዮን ማህበር እና በተወሰኑ ሰዎች አክሲዮን ለመሸጥ ለሕዝብ ጥሪ ሳያደርጉ የተቋቋመ አክሲዮን ማህበር ተብለው ሊከፋፈሉ ይችላሉ።[1] ይህ የአክሲዮን ማህበራት አከፋፈል በአክሲዮን ማህበር ምስረታ ወቅትም ሆነ ከምስረታ በኋላ በሚኖሩ የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያለው አንድምታ ከፍተኛ እንደሆነም ይታወቃል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አጭር ጽሑፍ ውስጥ ከሚነሳው ጉዳይ አንጻር በአክሲዮን ማህበር ምስረታ ሂደት ውስጥ የተለየ ቦታ ያላቸውን ሁለት ዓይነት ሰዎችን ማንሳት ያስፈልጋል። እነዚህ ሰዎች "አደራጆች" (Promoters) እና "መስራቾች" (Founders) በመባል የሚታወቁት ናቸው። በአዲሱ የንግድ ህግ ውስጥ ከተደረጉ ማሻሻያዎች ውስጥ በቀድሞው የንግድ ህግ እንዲሁም ልማድ ውስጥ "መስራቾች" እነማናቸው የሚለውን ብዥታ

---

[5297] LL. B, LL.M in Business and Corporate Laws, Advocate and Consultant at Law.

[1] የንግድ ህጉን አንቀጽ 248 እና 252 ይመለከቷል።

ለማስወገድ ታስበው የተካተቱት ድንጋጌዎችን መጥቀስ ይቻላል። በአዲሱ ንግድ ህግ መሰረት ሁለት ዓይነት ሰዎች በግልጽ ተለይተውና የራሳቸው ኃላፊነትና ጥቅም ተቀምጦላቸው ይገኛል። በእርግጥ በአዲሱ ንግድ ህግ ውስጥ ለመስራቾች የተሰጠ ልዩ ጥቅም የለም።[2] ይህንኑ ጉዳይ ግልጽ በሚያደርግ መልኩ የረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 7(2) መስራቾች በባለአክሲዮንነት ከሚያገኙት መብት ውጭ በመስራችነታቸው ምክንያት የሚከፈላቸው የአገልግሎት ክፍያ እንደማይኖር ያስቀምጣል። ነገር ግን ይህ የረቂቅ መመሪያው ክልከላ በንግድ ህጉ ውስጥ ለሚሸፈኑት ሁሉም መስራቾች ተግባራዊነት ይኖረዋል ወይ የሚል ጥያቄ ያስነሳል። ከታች ለማሳየት እንደተሞከረው በንግድ ህጉ ድንጋጌዎች መሰረት መስራቾች የሆኑ የተወሰኑ ሰዎች ልዩ ጥቅም ሊያገኙ የሚችሉበት ሁኔታ በረቂቅ መመሪያው ተፈጥሯል።

4. የንግድ ህጉ አንቀጽ 248(1) እንደሚያስቀምጠው አደራጅ የሚባለው፡- 1) አክሲዮኑ ለህዝብ ክፍት የሆነ ማህበር ምስረታን ያነሳሳ፣ 2) መግለጫ አዘጋጅቶ ሰዎች ማህበሩን እንዲቀላቀሉ የጋበዘ ወይም 3) የማህበሩን ምስረታ ዓላማ አድርጎ ይህንኑ ለማስፈጸም የተንቀሳቀሰ ሰው ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ማህበሩ የማይመሰረት ከሆነ ባለመመስረቱ ምክንያት ለሚመጣ ጉዳት ኃላፊነት መውሰድ አለበት። በንግድ ህጉ አንቀጽ 248(2) ላይ በግልጽ እንደተጠቀሰው አደራጅ አንድ ሰው ብቻ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም አደራጅ የማህበሩ ባለአክሲዮን ላይሆን ይችላል። አደራጅ ማነው ከሚለው ጥያቄ ጋር በተያያዘ አዲሱ የንግድ ህግ የፈጠረው ተጨማሪ ግልጽነት ቢኖር ከዚህ በላይ አደራጆች ተብለው ከተገለጹት ሰዎች ጋር በሚገቡት ውል መሰረት ክፍያ ለማግኘት ለማህበሩ ምስረታ አስፈላጊ የሆነ ጥናት፣ የሙያ ድጋፍና መሰል አገልገሎት ያቀረበ ባለሞያ አደራጅ አይባልም።

5. በሌላ በኩል በንግድ ህጉ ውስጥ መስራች የሚባለው አገላለጽ ጥቅም ላይ የሚውለው የተወሰኑ ሰዎች ለህዝብ ጥሪ ሳያደርጉ አስፈላጊውን መስፈርት በራሳቸው መካከል አሟልተው አክሲዮን ማህበር ሲመሰርቱ ነው። ይህንንም ከንግድ ህጉ አንቀጽ 252 የምንረዳው ነው። ከላይ እንደተባለው አደራጅ አንድ ሰው ብቻ መሆን የሚችል ሲሆን የመስራቾች ቁጥር ግን ቢያንስ አምስት መሆን ይኖርበታል። በእርግጥ በሌላ ህግ የመስራቾች አነስተኛ ቁጥር ከአምስት የበለጠ እንዲሆን ሊወሰን ይችላል።[3] ከዚህ ባለፈ የንግድ ህጉ የመስራቾችን ከፍተኛ ቁጥር አይወስንም። ነገር ግን ከታች እንደምንመለከተው ከንግድ ህጉ በተቃራኒ ረቂቅ መመሪያው የመስራቾችን ከፍተኛ ቁጥር ከ50 ሊበልጥ እንደማይችል ያመለክታል።

6. በንግድ ህጉ የተመለከተው የአክሲዮን ማህበራት (እንዲሁም በሂደቱ ተሳታፊ የሆኑትን ዋና ዋና ሰዎች) አከፋፈል ከላይ የተገለጸው ሲሆን በረቂቅ መመሪያው ውስጥ ከዚህ የተለየ የአከፋፈል መንገድ የተቀመጠ መሆኑን ማየት ይቻላል። ረቂቅ መመሪያው አክሲዮን ማህበራትን **"የህዝብ አክሲዮን ማህበር"** እና **"የግል አክሲዮን ማህበር"** በሚል

[2] ጉዳየን ግልጽ በሚያደርግ መልኩ የረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 7(2) መስራቾች በባለአክሲዮንነት ከሚያገኙት መብት ውጭ በመስራችነታቸው ምክንያት የሚከፈላቸው የአገልግሎት ክፍያ እንደማይኖር ያስቀምጣል።
[3] ንግድ ህጉ አንቀጽ 252(2)።

ይከፋፍላቸዋል፡፡ በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 2(4) እና 2(5) ጣምራ ንባብ መሰረት **የህዝብ አክሲዮን ማህበር** ማለት

> *ቁጥራቸው ከሃምሳ ባለአክሲዮኖች በላይ ያሉት የአክሲዮን ማህበር ወይም የአባላቱ ቁጥር የቱንም ያህል ቢሆን አክሲዮኖቹን ለሕዝብ በመሸጥ የተቋቋመ ማህበር ወይም አክሲዮኖቹ ለሕዝብ ክፍት የሆነ የአክሲዮን ማህበር ነው፡፡*

7. በዚህ ትርጉም መሰረት በረቂቅ መመሪያው ውስጥ ሶስት ዓይነት የአክሲዮን ማህበራት የህዝብ አክሲዮን ማህበር እንደሆኑ ተመልክቷል፡፡[4] በእርግጥ አክሲዮኖቹን ለሕዝብ በመሸጥ በተቋቋመ አክሲዮን ማህበርና አክሲዮኖቹ ለሕዝብ ክፍት በሆነ የአክሲዮን ማህበር መካከል ያለው ልዩነት ግልጽ አይደለም፡፡[5] እዚህ ጋር ትኩረት መስጠት የተፈለገው ጉዳይ ቁጥራቸው ከ50 ባለአክሲዮኖች በላይ ያሉት የአክሲዮን ማህበር የህዝብ አክሲዮን ማህበር የተባለበትን አግባብ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው የንግድ ህጉ የአክሲዮን ማህበራትን በሁለት ሲከፍል የባለአክሲዮኖችን ብዛት ከግምት ውስጥ አያስገባም፡፡ በመሆኑም የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች አምስት ብቻ እንኳን ቢሆን ማህበሩ ሲቋቋም አክሲዮን ለመሸጥ ለህዝብ ጥሪ አድርጎ ከሆነ ማህበሩ ለሕዝብ ክፍት የሆነ የአክሲዮን ማህበር ነው፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ብዛት ከ50 በላይ ቢሆንም ማህበሩ ሲቋቋም አክሲዮን ለመሸጥ ለህዝብ ጥሪ ካልተደረገና ባለአክሲዮኖቹ አስፈላጊ መስፈርቶችን በመካከላቸው ብቻ አሟልተው ካቋቋሙት ማህበሩ የተወሰኑ ሰዎች ለሕዝብ ጥሪ ሳያደርጉ ያቋቋሙት አክሲዮን ማህበር ተብሎ ነው የሚታወቀው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ረቂቅ መመሪያው ይህንን የአክሲዮን ማህበር የአከፋፈል ስርዓት የተከተለ አይደለም፡፡ ይህንን ሀሳብ የበለጠ ለማጠናከር መመሪያው "**የግል አክሲዮን ማህበር**" ለሚለው የሰጠውን ትርጉም መመልከትም ይቻላል፡፡ በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 2(4) እና 2(7) መሰረት የግል ማህበር ማለት፡-

> *ቁጥራቸው ከ5 እስከ 50 የሆኑ ሰዎች አክሲዮን ለመሸጥ ለሕዝብ ማስታወቂያ ሳያስነግሩ በመካከላቸው አስፈላጊውን ካፒታል በማዋጣት የሚመሰርቱት የአክሲዮን ማህበር ነው፡፡*

8. በዚህ ትርጉም መሰረት ከ50 በላይ የሆኑ ሰዎች በራሳቸው መካከል ብቻ የሚያቋቁሙት ማህበር የህዝብ አክሲዮን ማህበር ነው፡፡[6] ለህዝብ ማህበር የተሰጠውን ትርጉምም ለዚህ አባባል በደጋፊነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል የንግድ ህጉ በተወሰኑ ሰዎች መካከል አክሲዮን ለመሸጥ ማስታወቂያ ሳያስነግሩ የሚቋቋም ማህበርን በመስራቾች መካከል የተቋቋመ አክሲዮን ማህበር እንደሆነ ነው የሚናገረው፡፡ በሌላ አባባል ረቂቅ መመሪያው እንደ አደራጆችና መስራቾች የሚቆጥራቸው ሰዎች በንግድ ህጉ ከሚታወቁት የተለዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እዚህ ጋር መነሳት ያለበት ነጥብ ስለአክሲዮን ማህበር አመሰራረት የሚደነግገው

---

[4] በተጨማሪም የግል አክሲዮን ማህበር ከተመሰረተ በኋላ አክሲዮን ለሕዝብ የሸጠ እንደሆነ የሕዝብ ማህበር እንደሚሆን በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 7(4) ላይ ተቀምጧል፡፡

[5] ምናልባት *አክሲዮኖቹ ለሕዝብ ክፍት የሆነ የአክሲዮን ማህበር ነው፡፡*

[6] ይህ ማህበር ከተመሰረተ በኋላ አክሲዮን ለህዝብ የሸጠ እንደሆነ

*የረቂቅ መመሪያው* ክፍል ሁለት **“የህዝብ አክሲዮን ማህበራት ምስረታ”** *የሚመራው* በአደራጆች እንደሆነ *ይደነግጋል*።[7] በሌላ በኩል ደግሞ *የመመሪያው* አንቀጽ 7(1) **“የግል አክሲዮን ማህበር”** የሚመሰረተው በመስራቾች ይሆናል በሚል *ይደነግጋል*፡፡ ስለዚህ *መስራቾች* የሚባሉ ሰዎች የሚኖሩት የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ቁጥራቸው ከ50 ካልበለጠና ማህበሩም በመካከላቸው ብቻ ከተመሰረተ ይሆናል፡፡ ለዚህም ነው የረቂቅ *መመሪያው* አንቀጽ 2(8) *መስራች ማለት* “*የግል ማህበር በንግድ መዝገብ ሲመዘገብ በባለአክሲዮንነት የተመዘገበ ሰው ነው*” በማለት *ያስቀመጠው*፡፡

9. እዚህ *ጋር መታወስ ያለበት ጉዳይ መስራች* ወይም *አደራጅ ማነው የሚለው* ነጥብ ትልቅ *አንድምታ ያለው መሆኑ* ነው፡፡ ቢያንስ የንግድ ህጉ የተለየ ጥቅም የሚሰጠው ለአደራጆች ብቻ ነው፡፡[8] *ረቂቅ መመሪያውም መስራቾች* ልዩ ጥቅም የማግኘት መብት እንደሌላቸው *ይደነግጋል*፡፡ *ነገር ግን ረቂቅ መመሪያው* ለህዝብ አክሲዮን ማህበርና ለግል አክሲዮን *ማህበር* የሰጠው ትርጉም *መስራች መሆን* የሚገባቸውን ሰዎች አደራጆች *ሊያደርጋቸው* የሚችልበት *አጋጣሚ ሰፊ* ነው፡፡ ይህ ደግሞ በህግ አውጪው *ያልተፈቀደን መብት* ለመስራቾች *ጭምር* የሚሰጥ ይሆናል፡፡ በእርግጥ የረቂቅ *መመሪያው* አንቀጽ 4 “**የሕዝብ ማህበር ምስረታ የሚመራው በአደራጆች ነው**” ሲል ምን ለማለት *ፈልጎ* ነው የሚለውን *ጥያቄ ማንሳት ያስፈልጋል*፡፡ ለዚህም *ጥያቄ መሰረት* የሚሆነው በረቂቅ *መመሪያው* ውስጥ **“የሕዝብ ማህበር”** እና **“የሕዝብ ማህበር ምስረታ”** የሚሉት *አገላለጾች* ለየራሳቸው ትርጉም የተሰጣቸው *መሆኑ* ነው፡፡ ለሕዝብ ማህበር የተሰጠውን ትርጉም ከላይ የተመለከትነው ስለሆነ እዚህ *ጋር መድገሙ* አስፈላጊ አይደለም፡፡ ስለሆነም **“የሕዝብ ማህበር ምስረታ”** የሚለውን ስንመለከት የረቂቅ *መመሪያው* አንቀጽ 2(6) የሚከተለውን ትርጉም እንዳስቀመጠ ማየት እንችላለን፡፡

> ***የሕዝብ ማህበር ምስረታ** ማለት አክሲዮኖችን ለሕዝብ ለመሸጥ በሚደረግ ማስታወቂያ ካፒታል በመሰብሰብ የሚደረግ የአክሲዮን ማህበር ምስረታ ነው፡፡*

10. ይህንን ትርጉም መሰረት አድርገን የሕዝብ ማህበር ምስረታ የሚመራው በአደራጆች ነው ሲባል ከንግድ ህጉ አንቀጽ 248 *ጋር የሚፈጠር* ግጭት አይኖርም፡፡ ምክንያቱም በዚህ የረቂቅ *መመሪያው* አንቀጽ እና በንግድ ህጉ መሰረት አደራጆች ሚና የሚኖራቸው የሚመሰረተው የአክሲዮን ማህበር አክሲዮኖችን ለሕዝብ ለመሸጥ በሚደረግ ማስታወቂያ ካፒታል በመሰብሰብ የሚመሰረት በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡ *ነገር ግን* ይህ ሀሳብ የረቂቅ *መመሪያው* እውነተኛ ፍላጎት ነው ማለት *ያስቸግራል*፡፡ በመጀመሪያ የረቂቅ *መመሪያው* አንቀጽ 4 ርዕስ **የሕዝብ ማህበር አደራጆች** እንጅ **የሕዝብ ማህበር ምስረታ** የሚል አይደለም፡፡ የመመሪያው ፍላጎት የሚመስለው ከላይ በተገለጸው ትርጉም መሰረት የሕዝብ አክሲዮን ማህበር የሚላቸው ማህበራት በሙሉ ምስረታቸው የሚመራው በአደራጆች እንዲሆን ነው፡፡ ይህ ካልሆነ አደራጆችም ሆኑ መስራቾች የማይመሯቸው የአክሲዮን ማህበር ምስረታ ሂደቶች ይኖራሉ እንደ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ብዛታቸው ከ50 ሰዎች በላይ

---

[7] የረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 4፡፡
[8] ንግድ ህግ አንቀጽ 253፡፡

የሆኑ ባለአክሲዮኖች አክሲዮን ለመሸጥ ለህዝብ ማስታወቂያ ሳያወጡ በራሳቸው መካከል ብቻ ካፒታል በማሰባሰብ የሚመሰርቱትን የአክሲዮን ማህበር ምስረታ የሚመሩ ሰዎች አደራጆች ወይም መስራቾች አይሆኑም፡፡

### 3. ማጠቃለያ፡-

11. በዚህ አጭር ጽሑፍ ውስጥ ለማንሳት እንደተሞከረው ረቂቅ መመሪያው አክሲዮን ማህበራትን የከፋፈለበት መንገድ በአዲሱ የንግድ ህግ ውስጥ ከተመለከተው የተለየ ነው፡፡ በዋናነት ረቂቅ መመሪያውና የንግድ ህጉ አደራጆችና መስራቾች እነማን ናቸው በሚለው ጉዳይ ላይ ልዩነት አላቸው፡፡ ይህ ደግሞ በሁለቱ ጽንሰ ሀሳቦች ላይ በንግድ ህጉ የተፈጠረውን ግልጽነት የሚያደበዝዝ ይሆናል፡፡ ስለሆነም መመሪያው ከአዋጁ ሊጣረስ ስለማይችል የአክሲዮን ማህበራትን ዓይነትም ሆነ አደራጆችንና መስራቾችን በተመለከተ በመመሪያው ድንጋጌዎች ላይ አስፈላጊው ማሻሻያ ሊደረግ ይገባል፡፡

12. ምናልባት ብዙ ባለአክሲዮኖች ያላቸውን የአክሲዮን ማህበራት እንደ የህዝብ ማህበር መቁጠሩ በምስረታም ወቅት ሆነ ከምስረታ በኋላ ለሚኖር መንግስታዊ ቁጥጥርና ክትትል አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡[9] ነገር ግን ይህንን ለማድረግ አግባብነት ካላቸው የንግድ ህጉ ድንጋጌዎች ጋር የተጣጣሙ ድንጋጌዎች ያሉት መመሪያ ማዘጋጀት ይገባል፡፡ ለምሳሌ ጉዳዩ ከሚይዘው የህዝብ ጥቅም (public interest) አንጻር ምንም እንኳን ለህዝብ አክሲዮን ሳይሸጡ በራሳቸው መካከል ያቋቋሙት የአክሲዮን ማህበር ቢሆንም ባለአክሲዮኖቹ ብዛት ያላቸው ከሆነ የሚመለከተው አካል የምስረታ ሂደቱን በቅርበት የሚከታተልበትን ስርዓት መዘርጋት ሊኖርበት ይችላል፡፡ ይህንን ሲያደርግ በአዋጁ አደራጅ ያልሆኑ ሰዎችን አደራጆች የሚያደርግ ስርዓት እንዳይፈጠር ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በመስራቾች መካከል አክሲዮን ማህበር ሲቋቋም በዋናነት አሳሳቢ የሚሆነው የሚመሰረተው አክሲዮን ማህበርና ሶስተኛ ወገኖች ጉዳት ላይ እንዳይወድቁ ነው፡፡[10] ስለሆነም በዋናነት ይህንኑ ማዕከል ያደረግ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት መዘርጋት እንጂ በንግድ ህጉ መሰረት መስራች ለሆኑ ሰዎች ልዩ ጥቅም መፍጠር አያስፈልግም፡፡ ይህም የሆነው በመመሪያው አንዳንድ ድንጋጌዎች መሰረት መስራች መሆን የሚገባቸው ሰዎች እንደ አደራጆች ሊቆጠሩ የሚችሉበት አግባብ ያለ በመሆኑ ነው፡፡

---

[9] እንዲህ አይነቱ ሀሳብ በረቂቅ መመሪያው ውስጥም ተንጸባርቋል፡፡ የረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 13 በጠቅላላ ጉባኤ ወቅት ስለሚኖር የድምጽ አቆጣጠር ስርዓት ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም አንቀጽ 18 የሚመለከተው የመንግስት አካል የህዝብ አክሲዮን ማህበራት በሚያደርጉት ማንኛውም ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በታዛቢነት ሊገኝ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ አንቀጽ 19 ደግሞ በሕዝብ አክሲዮን ማህበር ውስጥ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ የሚከናወንበትን ስርዓት ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ተግባራት ሁሌ በንግድ ህጉ የተቀመጠውን የአክሲዮን ማህበራት አከፋፈል እንዲሁም ስለአደራጆችና መስራቾች ማንነት የተደነገገውን ባልተቃረነ መልኩ የሚደረጉበትን ስርዓት መፍጠር የማይቻል አይሆንም፡፡

[10] ይህንንም ከንግደ ህጉ አንቀጽ 250 እና 252 መረዳት ይቻላል፡፡